

# አባ ገብርኤል
## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ
## Abba Gabriel Archbishop
### In Ethiopian Orthodox Church



የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ"

"እግዚአብሔርም የእስራኤላውያንን የልቅሶአቸውን ድምፅ ሰማ" (ዘፀ. 2 ፥ 24)

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት በሙሉ። የእግዚአብሔርን ታላቅ ምሕረት የምንሻ በጊዜያውያን የኢትዮጵያ ገዢዎች በመረገጥ በመጨቆን በመታሰርና በመገደል ስላለው ሕዝባችን አጥብቀን እንጸልይ። ጭቆናው ፥ እስራቱና ግድያው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይወገድ ዘንድ በጾም በጸሎት የሦስት ቀን ሡባዔ እናድርግ። ስለተጨቆነው ሕዝባችን እንደ ነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ድምጻችንን እናሰማ ፤ እንደ ራሄልም ስለ ልጆቻችን እናልቅስ ፤ እያለቀስንም እንባችንን ወደ እግዚአብሔር እንርጭ። "ልባችንንም ከእጃችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣ" (ሰቆቃወ ኤርምያስ 3 ፥ 41)

መሐሪ አምላክ ወደ ነነዌና ወደ ነነዌ ሰዎች ተመለከተ። የነነዌ ሰዎች ቁጥር ከአንድ መቶ ሃያ ሺ በላይ ነበረ። ከሠሩት እጅግ አስነዋሪ ኃጢአትም የተነሣ እግዚአብሔር የነነዌን ሰዎች ሊደመስሳቸው ፈለገ ነገር ግን የነነዌ ሰዎች ሰባኪና አስተማሪ ስላልተላከላቸው መሪዎቹም ተመሪዎቹም በደል መፈጸማቸውን የተመለከተእግዚ አቤር እነሱን ከማጥፋቱ በፊት ንስሐን የሚሰብክላቸው ሰባኪ ለመላክ ወሰነ። በ770 ዓመተ ዓለም የነበረው ዮናስ በእግዚአብሔር ተመረጠና ተጠራ "ሂድ ለነነዌ ኃጢአተኞች ከመደምሰሳቸው በፊት በንስሐ ከክፉ ኃጢአታቸው ይመለሱ እንደሆነ አጥብቀህ አስተምራቸው" ብሎ አዘዘው። የአማቴ ልጅ ዮናስ ግን የእግዚአብሔርን ጥሪ ባለመስማት ትእዛዙንም ባለመቀበል ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ወደ ኢዮጴ ሄደ። ከዚያም በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ተርሴስ ለመሸሽ ጉዞውን ቀጠለ።

ከእግዚአብሔር ፊት መሸሽ ከቶ አይቻልምና ከእግዚአብሔርም ሸሽቶ ማምለጥ አይሞከርምና ዮናስ የተሳፈረባት መርከብ በከባድ ማዕበል ተመታች ፤ በዚያን ጊዜ "መርከቢቱ በሞገድ መመታት በእኔ በደል ነውና እኔን ወደ ባሕሩ ጣሉኝ" ብሎ በመርከቢቱ የነበሩትን ሰዎች ለመናቸው። እነሱም ከመርከብ ገፍትረው ወደ ባሕር ጣሉት። በዚያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ታላቅ ዓሣ አንበሪ ትእዛዝ አፍራሹን ዮናስን ዋጠው። ነገር ግን አልበላውም። በፈጣሪ የታዘዘው ዓሣ አንበሪ እንደ መርከብ፣ ዮናስ እንደተሳፋሪ ሆነው በእግዚአብሔር መሪነት ከነነዌ ከተማ ባሕር ዳር ደረሱ። ዮናስ ተተፋ፣ ዓሣውም ዮናስን ተፍቶ ወደ ዓለሙ (ወደ ባሕሩ) ተመለሰ። በእግዚአብሔር ተገድዶ ወደ ነነዌ የገባው ዮናስ ወደ ከተማው ውስጥ ገብቶ እየጮኸ መስበክ ጀመረ። "ሁላችሁም በአፋጣኝ ንስሐ ካልገባችሁ ፤ በንስሐ ካልተመለሳችሁ ነነዌ በሦስት ቀን ውስጥ ትገለበጣለች" እያለ የንስሐ ስብከት ሰበከ። "ካልተመለሳችሁ በሦስት ቀን ትደመሰሳላችሁ ብሏል እግዚአብሔር" እያለ ተናገረ።



2600 S.Veitch St. #105 Arlington,VA 22206 Tel. (703) 746 0777 Fax. (703) 746 0558

በዚያን ጊዜ የነነዌ ሰዎች ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ነዋሪ ድረስ ሁሉም በጾምና በጸሎት ተወስነው ለሦስት ቀናት በንስሐ እግዚአብሔርን እንዲለምኑ አስቸኳይ አዋጅ ታወጀ። ሁሉም በጾም ፣ በጸሎትና በዕንባ እግዚአብሔርን ለመኑ ፤ እንስሳቱ ሁሉ ሦስት ቀን ከበረታቸው ሳይወጡ ከሕዝቡ ጋር በጾም ተወሰኑ። አጠቃላይ የንስሐ ጥሪና ሁሉን ያካተተ የሦስት ቀን ሡባኤ የጾምና የእንባ ምሕላ ተደረገ።

በዚህ ጊዜ መሐሪ እግዚአብሔር የሕዝቡን የንስሐ ጾምና ጸሎት ተቀበለ። ስለዚህም እግዚአብሔር ለነነዌና ለነነዌ ሕዝብ ምሕረቱን ሰደደላቸው። ሕዝቡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስለተመለሱ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ ከተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ ተመለሰ። ምሕረቱንና ሰላሙን ሰጣቸው። በዚያን ጊዜ በነነዌ ምሕረት ሰፈነ። (ትንቢተ ዮናስ ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አራት ያለውን ታሪክ ማንበብ ይገባል)

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ሆይ !

በሀገራችን በኢትዮጵያ በዮናስ ወንበር የተቀመጡ ነቢያት ፣ ማለት ብፁዐን አባቶችና ካህናት ሕዝቡን ለንስሐና ለጸሎት ማዘጋጀቱን (ማጸለዩን) ስለፈሩ ሕዝቡ ራሱ እና ሁላችን ሀገራችንን ከወደቁበት ከባድ ፈተና ለማዳን በእነዚህ የነነዌ ሰዎች በተጠቀሙባቸው ሦስቱ ቀናት እንዲሁም በመጪው ዐቢይ ጾም በእየ ቤተክርስቲያኑና አመቺ በሆነ ቦታና ሰዓት በልቅሶና በእንባ ወደ እግዚአብሔር እንድንጸልይና ከልብ ምሕላ እንድናደርግ በእግዚአብሔር ስም ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

ነገር ግን ወደ ፈጣሪያችን ለመጸለይና ለመለመን ሡባኤ ከመጀመራችን በፊት ቂምን ፥ በቀልን ከልባችን ማስወገድ አለብን። ቂም ይዞ ጸሎት ማድረግ ዋጋ ቢስ ነውና።

እግዚአብሔር አምላካችን የምናደርሰውን ጸሎት ፥ የምንጾመውንም ጾም ተቀብሎ ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በምሕረቱ በርኅራሔው ይኅብኝልን።

አሜን !

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አባ ገብርኤል
የኢትዮጵያ ኦ፣ተ፣ ቤተ ክርስቲያን
ሊቀ ጳጳስ